መልእክት ስምንት

## የዳዊት ዘር የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ 2 ሳሙ. 7፡12፣ 14፤
ማቴ. 22፡41-45፤ ሐዋ. 13፡23፣ 33፤ ሮሜ 1፡3-4፤ 8፡29፤ ራእ. 22፡16

**I. "ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ…እኔም አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል"—2 ሳሙ. 7፡12፣ 14፦**

ሀ. እዚህ ጋር *ዘርህ* በቀጥታ ሲተረጎም የሚያመለክተው የዳዊትን ልጅ ሰሎሞንን ነው—1 ነገ. 5፡5፤ 8፡15-20።

ለ. 2ኛ ሳሙኤል 7፡14ን በሚጠቅሰው በዕብራውያን 1፡5 *መሠረት*፣ የዳዊት ዘር መለኮትና ስብዕና ያለው የእግዚአብሔር በኵር ልጅ ክርስቶስ ነው—ዕብ. 1፡5፣ 6።

ሐ. በ 2ኛ ሳሙኤል 7፡12 *ዘርህ* የሚለው እና በቁጥር 14 *ልጅ* የሚለው (አ.መ.ት.) የሚያመለክተው የዳዊት ዘር የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆን፣ ማለትም፣ የሰው ዘር የመለኮት ልጅ እንደሚሆን ነው—ሮሜ 1፡3-4።

መ. የዳዊት ዘር የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚመለከተው ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ጠንካራ በሆነ መልኩ ቀጥሎ ዳብሯል—ማቴ. 22፡41-45፤ ራእ. 22፡16።

**II. በማቴዎስ 22፡41-45 ጌታ ኢየሱስ በአጽናፍ-ዓለም ውስጥ ታላቁን ጥያቄ ጠየቀ፦ "ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?"—ቁ. 42፦**

ሀ. ፈሪሳውያን ክርስቶስ የዳዊት ልጅ እንደሆነ ተናገሩ፣ ጌታም ዳዊትስ ጌታ ብሎ ከጠራው፥ እንዴት ልጁ መሆን እንደሚችል ጠየቃቸው—ቁ. 43-45።

ለ. ክርስቶስን ልናውቀው የምንችለው በእግዚአብሔር መገለጥ በኩል በመንፈሳችን ብቻ ነው—ቁ. 43፤ ኤፌ. 3፡5።

ሐ. ክርስቶስ አምላክ ነው፤ በመለኮትነቱ የዳዊት ጌታ ነው—ማቴ. 22፡43።

መ. ክርስቶስ ሰውም ጭምር ነው፤ በስብዕናው የዳዊት ልጅ ነው—ቁ. 42፣ 45።

**III. በራእይ 22፡16 ጌታ ኢየሱስ "እኔ የዳዊት ሥር እና ዘር ነኝ" አለ፦**

ሀ. በመለኮትነቱ፣ ክርስቶስ የዳዊት ሥር፣ የዳዊት ምንጭ ነው፤ በስብዕናው ክርስቶስ የዳዊት ዘር፣ ከዳዊት የተገኘ ነው።

ለ. እንደ የዳዊት ሥር ክርስቶስ ጌታ ነው፣ እንደ የዳዊት ዘር የዳዊት ልጅ፣ የዳዊት ቁጥቋጥ ነው፤ *የዳዊት ዘር* ጌታ ሰው እንደሆነ እና ከዳዊት እንደወጣ እንደሚያመለክት እንዲሁ፣ *የዳዊት ሥር* እርሱ አምላክ እንደሆነ እና ዳዊት ከእርሱ እንደወጣ ያመለክታል።

ሐ. በራእይ 22፡16 ክርስቶስ ራሱ ሰውም አምላክም እንደሆነ፣ የስብዕና ባህሪ እና የመለኮት ባህሪ እንዳለው እውቅና ሰጥቷል።

**IV. በሐዋርያት ሥራ 13 ጳውሎስ ከዳዊት ዘር "እግዚአብሔር እንደ ተስፋው ቃል ለእስራኤል መድኃኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ" (ቁ. 23)፣ "ይህን ተስፋ እግዚአብሔር በሁለተኛው መዝሙር ደግሞ፦ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ኢየሱስን አስነሥቶ ለእኛ ለልጆቻቸው ፈጽሞአልና" (ቁ. 33) ብሏል፦**

ሀ. በቁጥር 32 እና 33 ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር በኵር ልጅ ለአባቶች ተስፋ ተገብቶ እንደነበር እናያለን፣ እግዚአብሔርም ኢየሱስን ከሞት በማስነሣት ይህንን ተስፋ ፈጸመው።

ለ. ትንሣኤ ለሰዉ ኢየሱስ ውልደት ነበር፦

1. በትንሣኤው በብዙ ልጆች መካከል የእግዚአብሔር በኵር ልጅ ለመሆን ከእግዚአብሔር ተወልዷል—ሮሜ 8፡29።
2. ከዘላለም ጀምሮ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ነበር—ዮሐ. 1፡18፤ 3፡16።
3. ከተሠገዎው በኋላ፣ በትንሣኤው በኩል የእግዚአብሔር በኵር ልጅ ለመሆን በስብዕናው ከእግዚአብሔር ተወለደ—ዕብ. 1፡6።

ሐ. ጳውሎስ በመዝሙር 2፡7 ውስጥ የጌታን ትንሣኤ ማየት ችሎ ነበር፦ "አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ"፦

1. ጳውሎስ "ዛሬ" የሚለውን ቃል ለጌታ ትንሣኤ ቀን ተጠቀመው።
2. ይህ ማለት የክርስቶስ ትንሣኤ እንደ የእግዚአብሔር በኵር ልጅ መወለዱ ነበር ማለት ነው።
3. ኢየሱስ፣ የሰው ልጅ፣ ከሙታን በመነሣት የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ተወለደ፤ ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን ማስነሣቱ የበኵር ልጁ እንዲሆን እርሱን መውለዱ ነበር—ሐዋ. 13፡33።

መ. በተሠግዎ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ስብዕናን ለበሰ እና አምላክ-ሰው ሆነ (ዮሐ. 1፡14፣ 18፤ ሉቃ. 1፡35)፤ ከዚያም በትንሣኤ ይህ አምላክ-ሰው የበኩር ልጁ ለመሆን ከእግዚአብሔር ተወለደ (ሐዋ. 13፡33፤ ዕብ. 1፡6፤ ሮሜ 8፡29)፦

1. ከተሠግዎ በፊት የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ የስብዕና ባህሪ አልነበረውም፤ መለኮታዊ ባህሪ ብቻ ነበረው።
2. በትንሣኤ የእግዚአብሔር በኩር ልጅ የስብዕና ባህሪ እንዲሁም መለኮታዊ ባህሪም አለው።

ሠ. በትንሣኤው ክርስቶስ በኲሩ ልጅ ለመሆን ተወለደ፣ በዚያኑ ጊዜም አማኞቹ ሁሉ የእግዚአብሔር ብዙ ልጆች ለመሆን ተወለዱ—1 ጴጥ. 1፡3፤ ዕብ. 2፡10፦

1. ከእነዚህ ብዙ ልጆች መካከል፣ በኲሩ ብቻ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ነው—ዮሐ. 1፡18፤ 1 ዮሐ. 4፡9።
2. ይህ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ፣ ከሞት በተነሣው ስብዕናው፣ የእግዚአብሔር በኩር ልጅም ጭምር ነው—ሮሜ 8፡29።
3. የበኲሩ ልጅ መለኮትም ስብዕናም አለው፣ እኛም አማኞቹ እንደ የእግዚአብሔር ብዙ ልጆች ሁለቱም ማለትም የስብዕና ባህሪ እና መለኮታዊ ባህሪ አለን—2 ጴጥ. 1፡4።

## V. በትንሣኤው በስብዕና ባህሪው የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ በኃይል የተሰየመውን ክርስቶስን ማወቅ ያስፈልገናል—ሮሜ 1፡3-4፦

ሀ. ከተሠግዎው እና ከትንሣኤው በፊት፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፣ አንድያው ልጅ ነበር—ዮሐ. 1፡18፤ 3፡16።

ለ. ክርስቶስ ከተሠግዎ በፊት የእግዚአብሔር ልጅ የነበረ ቢሆንም እንኳን፣ በተሠግዎ ከመለኮትነት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን የስብዕና ባህሪን ስለለበሰ በትንሣኤ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ መሰየም ያስፈልገው ነበር—1፡1፣ 14፤ ሮሜ 8፡3፦

1. የእግዚአብሔር ልጅ ሥጋ ከለበሰ በኋላ፣ መለኮታዊ ባህሪው በሥጋ ተሸፈነ።
2. ክርስቶስ በመለኮትነቱ አስቀድሞም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፣ የስብዕና ባህሪ ያለው፣ ከማርያም የተወለደው ኢየሱስ የነበረው ክፍሉ የእግዚአብሔር ልጅ አልነበረም—ሉቃ. 1፡31-32፣ 35።
3. ክርስቶስ በትንሣኤው የስብዕና ባህሪውን፣ ስብዕናውን ቀደሰው፣ ከፍም አደረገው፣ በዚህ የስብዕና ባህሪም በትንሣኤ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተሰየመ፤ እንዲሁም በትንሣኤው የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተወለደ—ሮሜ 1፡3-4፤ ሐዋ. 13፡33፤ ዕብ. 1፡5።
4. ይህ የእግዚአብሔር ልጅ መሰየም "በኃይል"፣ እውነታው መንፈስ በሆነው በክርስቶስ የትንሣኤ ኃይል ነበር—ሮሜ 1፡4፤ ፊልጵ. 3፡10፤ ኤፌ. 1፡19-20።

ሐ. በትንሣኤ በመሰየሙ በኩል ከተሠግዎው በፊት አስቀድሞም የእግዚአብሔር ልጅ የነበረው ክርስቶስ በአዲስ መንገድ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነ—ሮሜ 1፡4፦

1. ከተሠግዎው በፊት መለኮትነት ብቻ ያለው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፤ በትንሣኤው በኩል በመለኮትነትም በስብዕናም የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተሰየመ—ቁ. 4።
2. ክርስቶስ የስብዕና ባህሪን ባይለብስ ኖሮ፣ ከዘላለም ጀምሮ እንኳን በመለኮትነቱ የእግዚአብሔር ልጅ ስለነበር የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ መሰየም አያስፈልገውም ነበር—ዮሐ. 1፡18፤ 17፡5።
3. በተሠግዎ በኩል ስብዕናን በመልበስ፣ በትንሣኤ ባለ ስብዕና የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተሰየመ—1፡14፤ ሮሜ 8፡3፤ 1፡3-4፤ ዕብ. 2፡14፦
   ሀ. እንደተሰየመው የእግዚአብሔር ልጅ፣ ክርስቶስ ሁለት ባህሪያት አሉት፣ መለኮት እና ስብዕና፤ አሁን ያለው ስብዕና ተፈጥሮአዊ ስብዕና ሳይሆን በትንሣኤ ከፍ የተደረገ ስብዕና ነው—ሮሜ 1፡4።
   ለ. የክርስቶስ የስብዕና ባህሪም እንኳን የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተሰይሟል፣ ምክንያቱም በመለኮትነትም በስብዕናም የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተሰይሟልና።

መ. ክርስቶስ በስብዕና የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ መሰየሙ "እንደ ቅድስና መንፈስ" ነበር—ቁ. 4፦

1. የቅድስና መንፈስ በጌታ ኢየሱስ ውስጥ ያለ የሕይወት ውስጠ-ነገር ነው፤ በምድር ላይ በሥጋ ሲኖር፣ ይህ ውስጠ-ነገር በእርሱ ውስጥ ነበር—ማቴ. 1፡18፣ 20፤ ሉቃ. 1፡35።
2. ጌታ ኢየሱስ ከሙታን መካከል ሲነሣ፣ በውስጡ እንደነበረው እንደ ቅድስና መንፈስ ከሙታን በመነሣት በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ተሰየመ—ሮሜ 1፡4።
3. አሁን እርሱ መለኮታዊ ባህሪ እና ከሞት የተነሣ፣ የተለወጠ፣ ከፍ የተደረገ፣ የከበረ እና የተሰየመ የስብዕና ባህሪ ስላለው፣ አሁን እርሱ ከበፊቱ ይልቅ ይበልጥ ድንቅ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔር ልጅ ነው—6፡4፤ ሉቃ. 24፡26፤ ዮሐ. 17፡5፤ ሐዋ. 3፡13።

ሠ. ሮሜ 1፡3-4 እና 8፡29ን ማገናኘት ያስፈልገናል፦

1. በተሠግዎው፣ በመሰቀሉ እና በትንሣኤው፣ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ በኵሩ ልጅ ሆነ፣ የክርስቶስ ወንድሞች የሆኑት ብዙዎቹ ልጆች የእርሱን መልክ እየመሰሉ ነው—ዕብ. 2፡10-11፤ ሮሜ 8፡29።
2. በሮሜ 1፡3-4 የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ማራቢያው ሞዴል ሲሆን፣ በሮሜ 8፡29 ያሉት ብዙ ወንድሞች ደግሞ ከማራቢያ ሞዴሉ "በአንድ ግዜ-የፈሩ" እና በሕይወት በመዳን የበኵሩን ልጅ መልክ የሚመስሉት ናቸው።
3. ይህ መለኮት ወደ መደረግ ጉዳይ ያመጣናል እንዲሁም በኢኮኖሚው የእግዚአብሔር ውጥን በክርስቶስ እኛ፣ በክርስቶስ የምናምን አማኞች እና የእግዚአብሔር ልጆች፣ በሕይወት፣ በባህሪ እና በቅንብር (ተመላኪነቱን ሳይጨምር) አምላክ እንሆን ዘንድ ራሱን ሰው ማድረግ እንደሆነ ያመለክታል፤ እንዲህ ያለው ምልከታ እጅግ ታላቅ ነው፣ በመጨረሻም፣ መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ይጠናቀቃል—ቁ. 29፤ 1፡3-4፤ ዮሐ. 1፡1-13፤ 1 ዮሐ. 3፡1፤ ራእ. 21፡2፣ 10-11።

*© 2021 Living Stream Ministry*